# በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን

## ለአብነት ተማሪዎች የተዘጋጀ ስልጠና

**ጥቅምት 2011 ዓ/ም**

# መንፈሳዊ  መሪነት እና አስፈላጊነቱ

# መግቢያ

- እግዚአብሔር የዓለምን የታሪክ ሂደት የለወጠው በመረጣቸው ጥቂት ሰዎች ነው፡፡ **(Isaac Lim)**
- መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች፥
  - አብርሀም (ዘፍ. 12፥ 1-3) - ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ
  - ሙሴ (ዘጸ. 3፥1-12) - አሁንም ና፥ ሕዝቤን የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ ታወጣ ዘንድ ወደ ፈርዖን እልክሃለሁ።
  - ዳዊት (1ኛ ሳሙ. 13፥14) - እግዚአብሔር ዳዊትን የእስራኤል ንጉሥ አድርጎ ሾመው፡፡
  - አስቴር (መጽሐፈ አስቴር) - ሕዝቡን ለመጠበቅ አስቴርን እንደተጠቀመ

# ትር□ሜ

## መሪነት (Leadership) ምንድን ነው?

- አንድ ቡድን ፤ ድርጅት ወይም ማኅበረሰብን ለዓላማ መሳካት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ተፅዕኖ (Influence) የመፍጠር ሂደት ነው።

- “...መሪነት ማለት ሰዎችንና ሥርዓቶችን በማግባባት ትርጉም ያለውና ውጤት የሚያስገኝ ሁኔታ መፍጠር መቻል ማለት ነው። ...”

- “...መሪነት ማለት የሰዎችን እምነት/ አስተሳሰብና እንቅስቃሴ በማግባባትና በማሳመን መለወጥ ማለት ነው። ...”

- “...መምራት ማለት አንድ የሥራ መሪ ተከታዮቹን /ሠራተኞችን/ በማግባባትና በማስተባበር የድርጅቱን /የተቋሙን/ ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችል ተግባር ማከናወንና ለዚሁ ተግባር በግንባር ቀደምትነት መሰለፍ ማለት ነው። ...”

## ሥራ አመራር (Management) ምንድን ነው?

በሕግ ወይንም በሹመት በተገኘ ሥልጣን በመጠቀም የድርጅት ወይንም የቡድን አባላት በተፈለገው አቅጣጫ እንዲሄዱና የተጣለባቸውን ሓላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ የማድረግ ሒደት ነው።

## መምራትና ማስተዳደር

መምራትና ማስተዳደር የሚያመሳስሏቸው በርካታ ነገሮች ቢኖሯቸውም የየራሳቸው የሆኑ የተለያዩ ባሕሪያት አሏቸው፡፡ አንድነታቸውን እና ልዩነታቸውን ጠንቅቆ ያለማወቅ የተደበላለቀና የተሳሰተ ግንዛቤ እንዲፈጠር ስለሚያደርግ ችግሩን ለማስወገድ የሚያስችል መግለጫ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሀ/ መምራት (Leadership)፡-** ሰዎችን በማግባባት፣ በማሳመንና በማስተባበር ትክክለኛውንና ተፈላጊውን ውጤት ማስገኘት **(Doing The Right Thing)** ማለት ሲሆን፣

**ለ/ ማስተዳደር (Management)፡-** የድርጅት ዓላማ ለማሳካት እንዲቻል በትክክለኛው አሠራር ሥራን በማቀድ፣ በማደራጀትና በመቆጣጠር በሰዎች አማካይነት ማከናወን **(Doing Thing Right)** ማለት ነው፡፡

# መሪዎች (LEADERS) እና ሥራ አስኪያጆች (MANAGERS)

| መሪዎች | ሥራ አስኪያጆች |
|---|---|
| • ርእይ አላቸው | • ያቅዳሉ |
| • ሌሎችን ያነሳሳሉ | • ያደራጃሉ |
| • የጋራ እሴትን ይፈጥራሉ | • ይቆጣጠራሉ |
| • አዳዲስ ዐሳቦችን ያፈልቃሉ | • ይመራሉ |
| | |

| መሪዎች | ሥራ አስኪያጆች |
|---|---|
| • ተለዋዋጭ | • ግትር እና መመሪያን ይከተላሉ |
| • መልካም አጋጣሚዎችን ይፈልጋሉ | • ስጋቶች ላይ ትኩረት ይሰጣሉ |
| • ውጤት ላይ ያተኩራሉ | • ቅልጥፍና እዲሁም ብቃት ላይ ያተኩራሉ |
| • ያነቃቃሉ | • ይገመግማሉ ይቆጣጠራሉ |
| • ከሳጥኑ ዉጪ ያስባሉ | • ሐላፊነታቸዉ ላይ ብቻ ትኩረት ይሰጣሉ |
| • መንገድ ያሳያሉ | • ይከተላሉ |

## የመሪነት መሠረቶች

- ለመሪነት ዋነኛ መሠረት የሚሆኑት ራስ **(self)**፣ ቤተሰብ፣ ቡድን፣ ድርጅት /ተቋም/ ከባብያዊ ሁኔታና የለውጥ አመራር ናቸው፡፡

## ራስን መምራት

- ጆን ማክስዌል **(John Maxwell)** የተባሉ ምሁር "... ሞኝ ስንሆን ዓለምን ለመቆጣጠር እንፈልጋለን፡፡ ብልጥ ስንሆን ግን ራሳችንን እንቆጣጠራለን፡፡... ይላሉ፡፡"
- ራስን የመምራት ችሎታ ሥራን ወዲያውኑ ማከናወን፣ ከትንሽ ነገር መጀመርን፣ በዕቅድና በቅደም ተከተል አሠራር መሠረት መሥራትን፣ ለለውጥና ለአዲስ አስተሳሰብ ዝግጁ መሆንን ይጠይቃል፡፡

## ቤተሰብን /ቡድንን/ መምራት

- የተረጋጋና በራሱ የሚተማመን፣ ለዕውነት የቆመ ከራሱ አልፎ ቤተሰቡን፣ ሌሎች ሰዎችን አነስተኛ ስብስብ ያለውን ቡድን መምራት የሚለውን ይይዛል፡፡

## ድርጅትን /ተቋምን/ መምራት

- ድርጅት ማለት በአንድ ተቋም ውስጥ አንድን ግብ ለማሳካት የጋራ ጥረት እና ርብርብ የሚያደርጉ ሠራተኞች ወይም ግለሰቦች የሚለውን ይወክላል፡፡
- ድርጅትን መምራት ማለት የጋራ ዓላማን በታቀደ፣ በተቀነባበረና በተደራጀ ሁኔታ ለመከታተልና ለማስፈጸም የሚያስችል የራሱ የሆነ ሥርዐትና ደንብ ያለው በሰዎች የተደራጀ እንቅስቃሴ ማለት ነው፡፡

## የመሪነት ቁልፍ ተግባሮች

- የዋና ተጠሪነት ሚና (Figurehead)
- ተወካይነት (Spokesperson)
- ተደራዳሪነት (Negotiator)
- አሠልጣኝነትና አበረታችነት (Coach & motivator)
- የጋራ ቡድን መሥራችነት እና ገንቢነት (Team builder)
- ችግር ፈቺነት (Problem solver)
- አዲስና ገንቢ ፀሳብ አቅራቢነት (Entrepreneur)
- ስትራቴጂ ቀያሽነት (Strategic planner)

## የሥልጣን ምንጮች

የታወቁት የሥልጣን ምንጭ ዐይነቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

**ሀ/ ከሥራ ደረጃ የሚመነጩ (Position power)**

**1. አስገዳጅ ሥልጣን (Coercive power)**

- የመቅጣት፣ የማስገደድ ሥልጣንን የሚሰጥ ነው ፡፡

**2. የማበረታታት ሥልጣን (Reward Power)**

- የመሸለም፣ ዕድገት የመስጠት፣ ... ሥልጣንን የሚሰጥ፡፡

**3. ሕጋዊ ሥልጣን (Legitimate power)**

- በሥራ መደቡ ምክንያት የሚገኝ ተቀባይነት ያለው ሥልጣን፡፡

## ለ/ ከግል ሁኔታ የሚመነጩ (Personal Power)

## 1. ሙያዊ ሥልጣን (Expert Power)

- ግለሰቡ ካለው ልዩ ሙያና ዕውቀት አንፃር የሚገኝ ሥልጣን ነው፡፡

## 2. ተቀባይነት ያለው ሥልጣን (Referent power)

ከግለሰቡ ችሎታና ባሕርይ አንፃር በተከታዮቹ መደመጥንና መከበርን የሚያስገኝ ሥልጣን ፡፡

# የመሪነት ክሕሎቶች

አንድ መሪ ውጤታማ ትልቅ ወይንም የተሳካ መሪ ለመባል የሚከተሉትን ዐራት መሠረታዊ የመሪነት ክህሎቶች ሲኖሩት ብቻ ነው።

- ለተሰጠው ሥልጣን እና ሐላፊነት የሚጠይቀውን ትምህርት፤ ሥልጠና ዝግጅት እንዲሁም ልምድ ሊኖረው ይገባል።
- ሰዎችን በቀላሉ የማንበብና የመረዳት (Emotional Intelligence) ተሰጥኦ እና ጥበብ ሊኖረው ይገባል
- በመሪው ተጽእኖ ስር ያሉትን እና አጋሮች ያላቸውን ሀብት እውቀት ክህሎት እና በጎ አመለካከት እንዲሁም ልምድ በራሳቸው ተነሳሽነት እንዲያውሉ ተፅዕኖ መፍጠር ሲቻል።
- የተለያዩ የመሪነት ዘይቤዎችን ጠንቅቆ ያወቀ እና ለየሁኔታው የሚስማማውን ዘይቤ መጠቀም የሚችል መሆን አለበት።

## የመሪነት ብቃቶች (LEADERSHIP QUALITY)

- **ሙሉ ስብእና (Integrity) ያላቸው፣** ይህንንም ስንል መሪው የሚናገረውና የሚሠራው የማይጣረስ ሲሆን ከራሱ አቅም በተረፈ የድርጅቱን ወይም ሐላፊነት የጣለበትን ማኅበረሰብ ጥቅም የሚያስቀድም ታማኝ እና ቅን አገልጋይ ሊሆን ይገባል ።
- **የለውጥ ሐዋርያ (Change Agents)፡** መሪዎች እሴት የማይጨምሩባቸውን ልማዶች እና አስተሳሰቦች **(Belief System)** የሚያስወግዱ እና በየጊዜው ለራሳቸዉም እንዲሁም ለሌሎችም ለውጥን የሚያፋጥኑ እና ከፍተኛ ግለሰባዊ እና ተቋማዊ ለውጦችን የሚያመጡ ናቸዉ።

- **የቡድን ተጫዋች (Team Players)** በተናጥል ከመሥራት ይልቅ በቡድን መሥራትንና ሰዎችን በጋራ እንዲሠሩ የማስተባበር ብቃትና ክህሎት ያላቸው ናቸው
  - እንዲሁም የድርጅታቸዉን ወይንም ሐላፊነት የጣለባቸውን ማኅበረሰብ ዓላማ ለማሳካት ከወሳኝ አጋሮችና ቁልፍ ግለሰቦች ጋር መረብ የሚዘረጉ እና ግንኙነቱም ዘለቄታዊ እንዲሆን የሚያስችሉ ናቸው።

- **ፋናወጊ (Take Initiative)** በማንኛውም ሁኔታ ቀድመው የሚገኙ አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች እና ጉዳዮች ተስፋ የማይቆርጡ የቡድን ስሜት እንዳይሰበር እና ያጋጠማቸውን እንቅፋት በቁርጠኝነት የሚወጡ ናቸው።

- **ሰዎችን ያስቀድማሉ (People Centered)** ሁልጊዜ ለሰዎች ፍላጎት የሚጠነቀቁ አንድን ነገር በትእዛዝ ከማሠራት ይልቅ ሰዎች ፈልገው ሓላፊነት ተሰምቷቸዉ እንዲሠሩ የሚያደርጉ ናቸዉ።
- **ውጤታማ መሪነት እራስን ዝቅ በማድረግ (Professionalism with humility)** ዝቅ ያለ ዛፍ ፍሬ ያለው ነው እንዲሉ ዉጤታማ መሪዎች ሁልጊዜ እራሳቸዉን ዝቅ የሚያደርጉ እና ከኔ ይልቅ በኔ ስር ያሉት ሁል ጊዜ ትክክል ናቸው **(The subordinate is always right)** ብለው የሚያምኑ ናቸው።
  - ሆኖም ግን ዝቅ ማለታቸው በሌሎች እንደ መልፈስፈስ የማይቆጠርባቸው ይህን ማድረጋቸው ሁሉም ሥራን በአግባቡ እንዲሠሩ ለማድረግና የባለቤትነትን ስሜት መፍጠር መሆኑን የማስረዳት ብቃት ያላቸው ናቸው።

- **ሥልጣን በአግባቡ የሚጠቀሙ (Responsibility of using power)** መሪዎች የተሰጣቸውን ስልጣን በአግባቡ የሚጠቀሙ እና በሥልጣናቸዉ ለራሳቸዉ ጥቅም የማይሠሩ ሥልጣንን ከመጠቅለል (Power monger) ይልቅ ለሚመሩዋቸዉ ሥልጣንን የሚያጋሩ እና ሁል ጊዜም ተጠያቂነትን (Accountability) የሚያስቀድሙ ናቸው።
- **ለራሳቸውና ለጤናቸዉ ጊዜ የሚሰጡ (Health-Conscious)** መሪዎች እራሳቸውን አላስፈላጊ የሥራ ጫና ውስጥ የሚከቱ አይደሉም።

- ይልቁንም ሥራ እና ሐላፊነትን ለሌሎች በአግባቡ በማጋራት ስልታዊ በሆኑ ነገሮች ላይ የሚያተኩሩ እና ለራሳቸው ጊዜ የሚሰጡ ጤናቸውንም በአግባቡ የሚጠብቁ እንዲሁም ከምንም በላይ የነሱ መልካም ጤና መኖሩ ሥራቸውን በተገቢው ፍጥነት እና በሙሉ አቅም በመወጣት ወሳኝ መሆኑን የሚረዱ እንዲሁም ጤናቸው ከሚጎዳና መልካም ሰብእናቸዉን ከሚጓደል ከአላስፈላጊ ሱሶች እራሳቸውን የሚጠብቁ ናቸው።
- **ተተኪን ማፈራት የሚችሉ (EFFECTIVE IN SUCCESSION LEADERSHIP)** መሪዎች ሁልጊዜ ራሳቸውን ለድርጅቱ ወይንም ሐላፊነት ለሰጣቸው ማኅበር ብቸኛ አስፈላጊ ሰው አድርገው አይቆጥሩም
  - እኔ ሳልፍ ድርጅቱ ሊቀጥል ይገባል ለዚህም እንደ እኔ ወይንም ከኔ የሚበልጡ መሪዎችን መፍጠር ይቻላል ብለው የሚያምኑ የሚፈጥሩ ሁልጊዜ ለሌሎች ውጤታማ መሪዎች እና አዳዲስ ዐሳቦች እራሳቸውን ክፍት የሚያደርጉ ናቸው።

# የመሪነት ትግበራ (Practice of Leadership)

የመሪነት ትግበራ መሪዎች በምን አይነት ዘዴ መመሪያ መስጠት፤ ዕቅዶችን መተግበር እንዲሁም ሰዎች ማትጋት እና ማስተማር እንዳለባቸው አቅጣጫ ያሳያል።

- በመሆኑም ሦስት ዓይነት የመሪነት ትግበራ በተግባር ይታያሉ።
  - አምባገነናዊ መሪነት (Authoritarian or autocratic)
  - አሳታፊያዊ መሪ (Participative or

## አምባገነናዊ መሪነት (AUTHOCRATIC)

- ይህ አይነቱ  የመሪነት ዘይቤ መሪው የተከታዮቹን ዐሳብና ምክር ሳይጠይቅ አንድ ነገር እንዲተገበር አመራር ሲሰጥ የምናየው የመሪነት ትግበራ ነው፡፡
- ለአንዳንድ ሁኔታዎች አምባገነናዊ መሪነት ትክክለኛ እና ውጤታማ ዘዴ ሲሆን ይታያል፡፡
- ለምሳሌ መሪው ለውሳኔ የሚረዳው ትክክለኛ መረጃ ሲኖረው የድርጅቱን ወይም የቡድኑን አባላት ዐሳብ ለመጠየቅ ጊዜ ከሌለው ይህ ዐይነቱ ከመሪነት ዘይቤ አማራጭ የሌለው  ይሆናል፡፡
- ነገር ግን  ይህ ዐይነቱ የመሪነት ዘይቤ አልፎ አልፎ (Rear Occasions) ከላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች እና እንደ ጦር ሜዳ በመሳሰሉት ካልሆነ በስተቀር በዚህ ሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከኃይል (Muscle Power) ወደ እውቀት ተኮር አሠራር (Mind Power) በተቀየረበት ሁኔታ በዚህ አይነት የመሪነት ትግበራ የተመሪዎችን ትጋትና ቁርጠኝነት ማረጋገጥ አይቻልም፡፡

## አሳታፊ መሪነት (PARTICIPATIVE / DEMOCRATIC)

- በዚህ የመሪነት ትግበራ መሪው ከተመረጡ ወይንም ከሁሉም የድርጅት /የቡድን አባላት ጋር በመሆን በውሳኔ ሰጪነት ሒደት ውስጥ ይሳተፋሉ።
- ነገር ግን የመጨረሻውን ውሳኔ መሪው የመወሰን ሥልጣን አለው።
- ይህ ዘይቤ ትእዛዝ እንዲፈጸም ሳይሆን የሁሉንም ትብብር በመጠየቅ ለተወሰነው ውሳኔ ሁሉም ድርጅት ወይም የቡድን አባላት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ መልካም አጋጣሚን ይፈጥራል፡፡
- መሪው አሳታፊ በመሆኑ ተከታዮች እንደ ድንገት ሳይሆን እንደ ጠንካራ ጎን የሚቆጥሩት ሲሆን የበለጠ በመሪው ላይ ያለ ክብርና ታዛዥነት እንዲጨምር ያደርጋል።

## ልል መሪነት (LAISSEZ FAIRE / FREE REIGN)

- ከስሙ እንደምንረዳው ይህ ዐይነት የመሪነት ትግበራ ይበልጥ ለተመሪዎቹ ነጻነት የሚሰጥ ሲሆን መሪ በራሳቸው ውሳኔ እንዲወስኑ ያስችላል።
- ነገር ግን መሪው ለሚወስነው ውሳኔ ሐላፊነቱን ይወስዳል።
- ይህ ዐይነት የመሪነት ትግበራ ተመሪዎች ከፍተኛ የትምህርት ዝግጅት እና ልምድ ሲኖራቸው በአንዳንድ የምርምር ተቋማት እና ዩኒቨርስቲዎች አካባቢ ቢተገበር ይመከራል።

## መሪነትና ተከታይነት

### የተከታዮች አጠቃላይ ባህሪያት

- ጥሩ ተከታዮች፡- ራሳቸውን ከድርጅቱ /ከተቋሙ/ ዓላማ አንፃር በማየት የሚያስቡና በመሪያቸው በሚሰጣቸው አጠቃላይ አመራር መሠረት በራስ ተነሳሽነት ጭምር ተገቢውን እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ናቸው፡፡
- መጥፎ ተከታዮች፡- ሁልጊዜ ይህን አድርጉ ያንን አታድርጉ እስኪባሉ ድረስ የሚጠብቁ የቅርብ ክትትልና ቁጥጥር የሚያስፈልጋቸው ናቸው፡፡

ተከታዮች እንደ የባሕሪያቸው የተለያዩ ዐይነት የአመራር ዘይቤ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ለምሳሌ አዲስ ተቀጣሪ ከቆየውና ልምድ ካለው ሠራተኛ የበለጠ ክትትልና ድጋፍ ያስፈልጋዋል፡፡ ተነሳሽነት የጐደለው ሠራተኛ ከፍተኛ ተነሳሽነት ካለው ሠራተኛ የተለየ የአመራር ዘይቤ ያስፈልገዋል፡፡ አንድ መሪ የተከታዮቹን ተፈጥሮአዊ ስብእና ፍላጐታቸውን የሚያነሳሳቸውንና የማያነሳሳቸውን ሁኔታ፣ ... ወዘተ ለይቶ ማወቅ ይጠበቅበታል፡፡

- ተከታዮች ለመሪዎቻቸው ታማኝና ደፋር እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ ከተከታዮች የሚጠበቅ ድፍረት የሚከተለውን ያጠቃልላል፡፡
- ከመሪው የሚሰጥ አመራርን ከሓላፊነትና ከተጠያቂነት ጋር የመቀበል ድፍረት፣
- ተገቢውን ተግባር በመፈጸም መሪን የመደገፍ ድፍረት፣
- አግባብ ያልሆኑና ድርጅቱን የሚጐዱ የአመራር ተግባራትንና ሁኔታዎችን የመጋፈጥ ድፍረት፣
- በለውጥ ሂደት በንቃት የመሳተፍና ለውጡን የመደገፍ ድፍረት፣
- የተሻለ ዕድገት የሚያመጣ ለውጥን የማያራምድና የማይደግፍ አመራርን የመጋፈጥና አስፈላጊ ሲሆንም ትቶ የመውጣት ድፍረት የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## ሥነ ምግባርና የመሪነት ፈተና

- መሪዎች ሥነ ምግባርን የተላበሱና ለተከታዮቻቸው መልካም አርአያ እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ የተለያዩ ፈተናዎች ቢኖርባቸውም ፈተናዎቹን ሁሉ በአሸናፊነት መወጣት ይገባቸዋል፡፡ መሪነትን ከሚፈታተኑት ሁኔታዎች ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል-
- ሰዎችን በማግባባትና በማሳመን የሚሰጠው አመራር ለበጎ ተግባር ብቻ መዋል ያለበት የመሆን ፈተና፣

- መሪዎች ለተለያዩ መረጃዎች ከፍተኛ ቅርበት ያላቸው በመሆኑ መረጃዎቹን በመጠቀም በኩል ያለባቸው ፈተና፣
- መሪዎች ተከታዮቻቸው ለሚፈጽሟቸው ተግባሮች ሁሉ ሓላፊነት የመውሰድና ተጠያቂ የመሆን ፈተና፣
- የመሪዎች የሥልጣን አጠቃቀም ፈተና፣
- የማኅበራዊ የቁሳዊ ጥቅሞችና የመብቶች አጠቃቀም ፈተና፣
- የታማኝነት ፈተና፣
- በዐሳብ የመጽናት ፈተና፣ የመሳሰሉት ይገኙበታል።

# የመንፈሳዊ መሪ ሦስት መሠረታዊ መገለጫዎች

- መንፈሳዊ መሪነት ሦስት እኩል ጎን (equilateral triangle) ባለው ምስል ይወከላል።
- ይህ ምስል የጥንካሬና የመረጋጋት ምሳሌ ነው።
- ሦስቱ ጎኖች የመንፈሳዊ መሪን ሦስት መሠረታዊ መገለጫዎችን ይወክላሉ።

# የመንፈሳዊ መሪ ሦስት ጎን




አንድ መሪ ውጤታማ ለመሆን ሦስቱም መገለጫዎች መኖር አለባቸው።

## 1. መንፈሳዊ መሪ

- የመንፈሳዊ መሪና የዓለማዊ መሪ ልዩነቱ መንፈሳዊ መሪ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል “መንፈሳዊነትን የተላበሰ” መሆን መቻሉ ነው፡፡
- የእንቅስቃሴ ማእከሉም እግዚአብሔር ነው፡፡

# መንፈሳዊ መሪነት በሙሴ ሕይወት

1. **መንፈሳዊ መሪነት በእግዚአብሔር መጠራት ይጀምራል**
   - “እግዚአብሔር እርሱ ይመለከት ዘንድ እንደ መጣ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር ከቍጥቋጦው ውስጥ እርሱን ጠርቶ። ሙሴ፥ ሙሴ ሆይ አለ። እርሱም፦ እነሆኝ አለ።” **(ዘጸ. 3:4)**
2. **ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ተልእኮ**
   - አሁንም ና፥ ሕዝቤን የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ ታወጣ ዘንድ ወደ ፈርዖን እልክሃለሁ። **(ዘጸ. 3:10)**

3. **መንፈሳዊ መሪነት መንፈስ ቅዱስን ይከተላል**

– “ሙሴም ሚስቱንና ልጆቹን ወሰደ፥ በአህያ ላይም አስቀመጣቸው፥ ወደ ግብፅም አገር ተመለሰ ሙሴም የእግዚአብሔርን በትር ይዞ ሄደ።” (ዘጸ. 4:20)

4. **እግዚአብሔር ሁሉን ያስችላል**

– “እንግዲህ አሁን ሂድ፥ እኔም ከአፍህ ጋር እሆናለሁ፥ የምትናገረውንም አስተምርሃለሁ አለው።” (ዘጸ. 4:12)

5. **መንፈሳዊ ስጦታዎች ከሁሉም በላይ ናቸው**

- “እንዲህም ይሆናል እነዚህን ሁለት ምልክቶች ባያምኑ ቃልህንም ባይሰሙ፥ ከወንዙ ውኃን ውሰድ፥ በደረቁም መሬት ላይ አፍስሰው ከወንዙም የወሰድኸው ውኃ በደረቁ መሬት ላይ ደም ይሆናል።” **(ዘጸ. 4:9)**

6. **መንፈሳዊ መሪነት እግዚአብሔርን መምሰል ነው**

- ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው ነበረ። **(ዘኁ. 12:3)**
- “የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው።” **(ገላ. 5:22)**

# ዓለማዊና መንፈሳዊ መሪዎች፡ ንጽጽር

| ዓለማዊ መሪ | መንፈሳዊ መሪ |
|---|---|
| ➢በራሱ ይተማመናል | ➢በእግዚአብሔር ይመካል |
| ➢ሰዎችን ያውቃል | ➢እግዚአብሔርንም ያውቃል |
| ➢የመወሰን ክሕሎት አለው | ➢በእግዚአብሔር ፈቃድ መሠረት አድርጎ ይወስናል |
| ➢ጉጉት አለው | ➢ሥራ ላይ ያተኩራል፣ የተረጋጋ |
| ➢መንገድ ያሳያል | ➢የእግዚአብሔርን መንገድ ይፈልጋል፤ ይከተላል |
| ➢አዛዥ/ዲሞክራት | ➢ለእግዚአብሔር በመገዛት ይመራል |
| ➢ሰዋዊ በሆነ ነገር ይተጋል | ➢በእግዚአብሔርና በሰው ፍቅር ይተጋል |
| ➢ጥገኛ ያልሆነ | ➢በእግዚአብሔር  ጥገኛ የሆነ |

- መንፈሳዊ መሪነት መነሻው ከእግዚአብሔር ሲሆን መሪዎች የሚያድጉት (ውጤታማ የሚሆኑት) በእግዚአብሔር ነው።
- የመንፈሳዊ መሪነት ልምምድ እግዚአብሔርን ማእከል ያደረገ ሲሆን የመጨረሻ ግቡም እግዚአብሔርን ማመስገን/ማክበር ነው።

**“መንፈሳዊ መሪዎች መሪያቸው እግዚአብሔር እንደሆነ ይረዳሉ”**

*Henry and Richard Blackaby*

## 2. አገልጋይ መሪ

- መንፈሳዊ መሪዎች አገልጋይ መሪዎች መሆን አለባቸው
- እግዚአብሔር ሰውን የሚጠራው ለአገልግሎት ስለሆነ
- ስለዚህ አገልጋይ መሪነት መንፈሳዊ መሪነትን ይከተላል።

"ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ" (ፊል.**2:5-11)**

- አገልጋይ መሪ ማለት መሪነትን በአገልግሎት የሚያሳይ ነው።

"ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የሁሉ ባሪያ ይሁን" **(ማር. 10: 44)**

# የአገልጋይ መሪነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አርአያ

- መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ዝቅ አድርጎ እንደ አገልጋይ በመሆን ደቀ መዛሙርቱ እንደሱ እንዲያደርጉ ያስተምራቸው ነበር።

"... ከእራት ተነሣ ልብሱንም አኖረ፥ ማበሻም ጨርቅ ወስዶ ታጠቀ፤ በኋላም በመታጠቢያው ውኃ ጨመረ፥ የደቀ መዛሙርቱንም እግር ሊያጥብና በታጠቀበትም ማበሻ ጨርቅ ሊያብስ ጀመረ።"

(ዮሐ. 14፡2-5)

"እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ፥ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል። እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና።" (ዮሐ. 14፡14-15)

# አገልጋይ መሪ

- መሠረቱ፣ ኃይሉ/ብርታቱ እግዚአብሔር የሆነለት
- ከውስጥ የመነጨ የአገልጋይነት ስሜት
- ሠርቶ ማሠራት
- በፍቅር፣ ስለ ፍቅር

# 3. ሽግግራዊ መሪ

- መንፈሳዊና አገልጋይ ከመሆን ባሻገር መንፈሳዊ መሪዎች ሽግግራዊ ናቸው።
- ሽግግራዊ መሪዎች፣
- የለውጥ ሐዋርያ በመሆን የራሱን ዓለም ይለውጣል።
- ተከታዮቹን ወደ መሪነት ያሸጋግራል

# መሪዎች የለውጥ ሐዋርያ ናቸው!

# የተራራው ስብከት– ጥልቅ ለውጥ

- በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ላይ ያለው የጌታ ቃል 4 ዋና ዋና ነጥቦች

## 1. ያልተጠበቀን ነገር (ከተለመደው ለየት ያለ) ማድረግ

- ክርስቶስ የማይጠበቁ ሰዎችን "ብጹአን ናችሁ" ብለቸዋል።

- በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና። የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፥ መፅናናትን ያገኛሉና። የዋሆች ብፁዓን ናቸው፥ ምድርን ይወርሳሉና። ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፥ ይጠግባሉና። የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፥ ይማራሉና። ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፥ እግዚአብሔርን ያዩታልና። የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፥ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና። ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና። ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ። ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፥ ሐሴትም አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ አሳድደዋቸዋልና። *(ማቴ. 5:3-12)*

## 2. ከፍተኛ የሥነ ምግባር (ሞራል) ደረጃ፡

“እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ።” (ማቴ. 5፡48)

“ጽድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም።” (ቁጥር 20)

- የሚታወቁ ሕግጋትንም አጽን□ቸዋል። (ቁጥር 21-48)

## 3. የማይለወጥ እውነታን መሠረት ያደረገ ለውጥ፡

የእግዚአብሔር ሕግ እንደማይለወጥ አስረግጦ ነግረቸዋል።

- ክርስቶስ ያመጣው ለውጥ የእግዚአብሔርን ሕግ የሚተካ ሳይሆን ለመፈጸም ነው።

“እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም። እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ፥ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፥ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ። እንግዲህ ከነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር ለሰውም እንዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል፤ የሚያደርግ ግን የሚያስተምርም ማንም ቢሆን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል።” *(ቁጥር 17-19)*

4. የለውጥ ሐዋርያ ለመሆን የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች፡

“እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል? ወደ ውጭ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ወደ ፊት ለምንም አይጠቅምም። እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ። በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም።” (ቁጥር 13-14)

- ለውጥ ስለማምጣት መከራውን መታገስ እንዳለባቸው፣ በዚህም ለሌሎች ምሳሌ፣ መማሪያ መሆን እንዳለባቸው።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወለወላዲቱ ድንግል

ወለመስቀሉ ክቡር!